# ምክረ ሃሳቦች፡ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች በኢትዮጵያ

ይህ ምክረ ሃሳቦችን የያዘ ሰነድ አዲስ አበባ ውስጥና በኢንተርኔት ላይ የተካሄዱ ስብሰባዎችና አውደ ጥናቶች ውጤት ነው። እነዚህ የመፍትሄ ሃሳቦች ሰብዓዊ መብት ላይ ከሚሰሩ ባለሙያዎች በቀጥታ የተገኙ ናቸው። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከልና ጉዳታቸውን ለመቀነስ ብዙ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ይገኛሉ። ሲ.አይ.አር እነዚህን እንቅስቃሴዎች እንደየአስፈላጊነታቸው በዚህ ሰነድ ውስጥ አካቷል።

## በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ማለት ምን ማለት ነው?

“በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ማለት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በሙሉ ወይም በከፊል የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂዎችን ወይም ዲጂታል ሚዲያዎችን እንደ ጥቃት ማድረሻ፥ ማባባሻ እና ማሰራጫ በመጠቀም የሚፈፅሙት ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ማለት ነው“ (ዩ.ኤን.ኤፍ.ፒ.ኤ እ.ኤ.አ 2023)



www.infores.org/tfgbvinethiopia

## በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ጥናት ማካሄድ ለምንአስፈለገ?

የሰዎች ግላዊና ማህበራዊ ህይወት በኢንተርኔትና ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ በሠፊው እየተንፀባረቀ መምጣቱ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ አዲስ ፈተና ይዞ ብቅ ብሏል። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ስላደረጉ ጥቃቶችና ሴቶችን ኢላማ ስላደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ልዩነቶች ማጥናት የሴቶችን የኢንተርኔት ላይና ከኢንተርኔት ውጪ ደህንነት ለማስጠበቅ ያለሙ ፖሊሲዎችን ለማዘጋጀት መነሻ ይሆናል።

## በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን መከላል ለምን አስፈለገ?

ይህ ጥናት በኢንተርኔት ላይ ደህንነቱ የተጠበቀ መድረክ መፍጠር፣ ሴቶች በማህበራዊ ህይወት ላይላላቸው የተሟላ ተሳትፎ እገዛ ዘንደሚሰጥ አፅንዖት ሠጥቷል። ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ብዙ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች፣ በቴክኖሎጂ ድጋፍ በሚቃጡ ፆታን መሠረት ባደረጉ ጥቃቶች ምክንያት ዝምታን እንደመረጡና ኢንተርኔት ላይም ሆነ ከኢንተርኔ ውጪ ያላቸውን ማህበራዊ መስተጋብር እንደገደቡ ገልፀዋል።

ጥናቱን ለመመልከት

ይህንን ኮድ ስካን ያድርጉ

# መግቢያ

ኢትዮጵያ ውስጥ በቴክኖሎጂ ድጋፍ በሚቃጡ ፆታን መሠረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ የተሰራው ጥናት ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሴቶችና ልጃገረዶች ፆታዊ የጥላቻ ንግግርን ጨምሮ የተለያዩ አይነት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች እንደሚደርስባቸው አሳይቷል። በጥናቱ ግኝቶች መሠረት በኢንተርኔት ላይ ያለው የሴቶች ጥቃት ፤ ሴቶች በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊና ብሔር ተኮር ጉዳዮች ላይ ባላቸው ሚና ዙሪያ ያለውን የተዛባ ማህበረሰባዊ አመለካከት ያሳያል። በቴክኖሎጂድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል የሚቀረፁ ስትራቴጂዎች ዘላቂ ውጤት እንዲኖራቸው፣ የችግሩን ስርወ-መሠረት ያማከሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

## ቁልፍ ግኝቶች

- ሴቶችና ልጃገረዶች ከወንዶች የተለዩና በፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን፣ ስላቅንና ፌዝን የያዙ የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ይደርስባቸዋል።

- ብሔርና ሃይማኖት የመሳሳሉ ማንነቶች ከፆታ ጋር በተጨማሪነት ሲጠቁ ኢንተርኔት ላይ ያለው የሴቶች ደህንነት ስጋት ያጨምራል።

- ሴቶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮችእንደየማህበራዊ ሚዲያ መድረኩ በአይነት የተለያዩ ናቸው።

- ሴቶች ላይ ያነጣጠሩ የጥላቻ ንግግሮች ሌሎች ማንነቶችን ኢላማ ካደረጉ የጥላቻ ንግግሮች አንፃር የተለዩ እና የበታችነትን የሚሰብኩና በማህበራዊ ሚና ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የሚያንፀባርቁ ናቸው።

- በስብሰባዎችና በአውድጥናቶች ላይ የተደረጉት ምክክሮች ስለጥላቻ ንግግርና ተፅዕኖዎቹ በቂ ግንዛቤ መፍጠር አስፈላጊ እንደሆነ አሳይተዋል።

- ሴቶችና ልጃገረዶች በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የተሟላ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንተርኔት መድረክ አስፈላጊ እንደሆነ ይህ ጥናት አሳይቷል።

- ሴቶችና ልጃገረዶችን ኢላማ የሚያደርጉ የጥላቻ ንግግሮችን ልዩ ባህሪያት መረዳት ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ለሚቀረፁ ስትራቴጂዎች መነሻ ሆኖ ያገለግላል።

## የጥናቱ ዓላማ

- ኢትዮጵያ ውስጥ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ያለውን ማስረጃ ማጠናከር
- የመንግስት ተቋማት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎችና ማህበረሰቡ በቴክኖሎጂ ድጋፍ ስለሚቃጡ ፆታን መሠረት ስላደረጉ ጥቃቶች ያላቸውን ግንዛቤ ማሻሻል
- በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን በመከላከል ዙሪያ ለሚሰሩ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የመንግስት ተቋማት ተግባራዊ ምክረ ሃሳቦችን ማቅረብ

## ምክር ሃሳቦች

1. ትምህርት
2. ህግና ፖሊሲ
3. ማህበረሰብ-መር ምላሾች
4. የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ተጠያቂነት
5. የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘመቻዎች
6. ሴቶችና ልጃገረዶችን መደገፍ
7. ቀጣይነት ያላቸው ጥናቶች

# 1. ትምህርት

በስብሰባዎችና አውድ ጥናቶች ላይ የተደረጉት ውይይቶች፤ በፆታዊ እኩልነት፣ በጥላቻ ንግግርና ሌሎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ ስለሚቃጡ ፆታን መሠረት ስላደረጉ ጥቃቶችና ተፅዕኖቻቸው ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር አስፈለጊ እንደሆነ አሳይተዋል። የሚሰጡትም ትምህርቶች የጥቃት ፈፃሚዎችንና ተመልካቾችን ባህሪ በመቀየርና የጥቃት ሰለባዎችን ከለላ በመስጠት ላይ ያተኮረ መሆን አለበት። ስለትምህርቶቹና የትምህርቱ ኢላማ ቡድኖች እንደሚከተለው ቀርቧል።

## ኢላማ ቡድኖች

አሁን ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች ትምህርት ቤትና ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ባሉ ወጣቶች ላይ ያተኮሩ ናቸው። እነዚህ ዘመቻዎችን በማስቀጠልና በማስፋፋት ሌሎች የማህበረሰብ ቡድኖች ጋር እንዲደርሱ ማድረግ ያስፈልጋል። የቃለመጠይቅ ተሳታፊዎች ለሲ.አይ.አር እንደገለፁት፣ ኢንተርኔትላይ የሚታዩት ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ከኢንተርኔት ውጪ ባሉ ዋና ሚዲያዎች፣ የቴሌቪዥን ፕሮገራሞችና ማስታወቂያዎች ላይ ያሉትን ትርክቶች የሚያንፀባርቁ ናቸው። የውይይቱ ተሳታፊዎች ተፅዕኖ ፈጣሪ ለሆኑ ግለሰቦች የአሰልጣኞች ስልጠና እንደሚያስፈልግና የስራ ቦታዎች የሴት ባልደረባዎችን ከፆታዊ ጥቃቶች ለመከላከል በቂ ፖሊሲ እንደሌላቸው ገልፀዋል።

- ወጣቱ ማህበረሰብ (ትምህርት ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች)
- ሚዲያዎች (ጋዜጠኞችናአርታዒዎች)
- የማስታወቂያ ባለሙያዎች/የፊልም አዘጋጆች
- አክቲቪስቶችና ታዋቂግለሰቦች
- አስተማሪዎች (መምህራንና የሃይማኖትአባቶች)
- ህግ አስከባሪዎች (ዳኞች፣ጠበቃዎችና ፖሊስ)

## የትምህርት ዘመቻዎች

### በፆታ ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ አመለካከቶችን መከላከል

በፆታ እኩልነትና ሰብዓዊ መብች ላይ ያተኮሩ ትምህርቶች አስፈላጊ የሆኑና በትምህርት ቤት በሚሰጡ ትምህርቶች ውስጥ መካተት ያለባቸው ናቸው። የአውድ ጥናት ተሳታፊዎች እንደገለፁት ስለሴቶች መብት መታገል እንደ ምዕራባዊያን ሃሳብ ይቆጠራል። ሆኖም ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ሴቶችና ልጃገረዶች የተለያዩ አይነት ሚናዎችን ይጫወታሉ። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ማህበረሰብ ላይ የተመረኮዙ ትምህርቶች የፆታ እኩልነት ኢትዮጵያዊ እሴቶች መሆኑን ሊያሳዩ ይችላሉ። ሴታዊት በፆታ ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ ልማዶችን ለመሞገት ተከታታይነት ያላቸው አውድ ጥናቶችን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያካሄዳል።

### በጥላቻ ንግግር ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጫዎች

በጥላቻ ንግግር ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ አመለካቶች አንዳንድ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች ትኩረት እንዳይሰጣቸው ማድረጉን በአውደ ጥናቶች ተመልክተናል። በተጨማሪም በፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙ ንግግሮች፣ ስድቦች፣ አዋራጅ ግግሮችና አሳናሽ ቃላት፤ ዛቻና ጠብጫሪ ከሆኑ ንግግሮች አንፃር ያነሰ ጉዳት ያደርሳሉ የሚል አስተሳሰብ አለ። ስለ ጥላቻ ንግግርና ፆታዊ ጥቃት ምንነትና ተፅዕኖዎቹ የተሻለ ግንዛቤ መፍጠር አስፈላጊ ነው።

### የሚዲያ አጠቃቀም ክህሎት ማዳበር ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞች

የሚዲያ አጠቃቀም ክህሎት ማዳበር ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞች ስነ-ፆታዊ ጉዳዮችን ማካተት ይኖርባቸዋል። በማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ዘንድ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም እውቀትን፣ ጥልቅ እሳቤንና የትንታኔ ግንዛቤን ማዳበር፣ ግለሰቦች በመረጃ ተዓማኒነት ዙሪያ ያሉ ፈተናዎችን እንዲያልፉ ያግዛል። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትምህርት መስጠት ግለሰቦች ሴቶችን የሚያሳንሱና የሚያዋርዱ ቋንቋዎችን እንዲሞግቱ ያግዛል። ለምሳሌ መርሳ ሚዲያ ኢንስቲትዩት የነፃ ሚዲያና የመረጃ እውቀት ስልጠናዎችን የሚያበረታቱ ስራዎችን ይሠራል።

## ትኩረት




Article35




CARD
የመብቶች እና ዲሞክራሲ ዕድገት ማዕከል
CENTER FOR ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY
MEDIA LITRACY




Media Smart Youth Ethiopia
Empowered and responsible

# 2. ህግና ፖሊሲ

ሰዎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች የኢንተርኔት ውጪ ጥቃቶችን ያህል አደገኛ አይደሉም ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። ሆኖም ግን የአውድ ጥናቱ ተሳታፊዎች እነዚህ ወንጀሎች አደገኛና ግላዊ እንደሆኑ ገልፀዋል። የጥቃቱ ሰለባዎች በቤታቸው ምናልባትም ሶፋቸው ላይ ወይም አልጋቸው ውስጥ ሆነው በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ሊደርስባቸው ይችላል። ይህም ማለት ጥቃት አድራሾቹ የተጠቂዎቹን የግል መኖሪያ ደፍረዋል ማለት ነው።ህጎችና ፖሊሲዎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን በትኩረት እንዲያዩ ማድረግ በኢንተርኔት ላይና ከኢንተርኔት ውጪ የሴቶችን ደህንነት ለማስጠበቅ ወሳኝ ነው።

## ስልቶች

### ተሃድሶ

አሁን ላይ ያሉት ህጎችና ፖሊሲዎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት የደረጉ ጥቃቶች ያማከሉ አይደሉም። የፍትህ ስርዓቱ ነባሩን ህግ በመገምገም ለሴቶችና ልጃገረዶች የተሻለ ከለላ መስጠት ይገባዋል። አሁን ላይ ያሉት ህጎች በኢንተርኔት ላይና ከኢንተርኔት ውጪ ባሉ ጥቃቶች መካከል ልዩነቶችን ባያስቀምጥም ይህ ለተግባራዊነት እንደ እንቅፍት ሊታይ አይገባም።

### ማዳበር

የፍትህ ስነስርዓቱ የኢንተርኔት ላይ ትንኮሳዎችን፣ ፆታዊ ጥላቻ ንግግሮችን እና የበቀል ፖርኖግራፊን ጨምሮ ሌሎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን እንደወንጀል የሚደነግጉ ህጎችን ማርቀቅና አዳዲስ ህጎች ኢንተርኔትንና በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ያማከሉ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ተቋማት በስራ ቦታ ላይ ያሉ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችንና ትንኮሳዎችን (ኢንተርኔት ላይና ከኢንተርኔት ዉጪ) ለመከላከል የሚያግዙ ፖሊሲዎችን እንዲያረቁ የሚያበረታቱ መንግስት መር የሆኑ ፖሊሲዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ መርሳ ሚዲያና ካርድን (CARD) ጨምሮ ጥቂት ተቋማት እነዚህን ፖሊሲዎች አዘጋጅተዋል፡፡

አዳዲስ ህጎች ሲወጡ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸዉ ግለሰቦችን ጨምሮ ኢትዮጵያዊ ባለሙያዎችን፣ ሙያዊ ተቋማትንና በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታዊ ጥቃትን ለመከላከል የሚሰሩ ግለሰቦችንና አክቲቪስቶችን ማማከር ያስፈልጋል፡፡

### መጠቆም

ዉጤታማ የሆኑ የጥቆማ ዘዴዎች አለመኖራቸዉ ሴቶችና ልጃገረዶችን ስጋት ላይ ጥሏል፡፡ በእነዚህ ጥቆማ ዘዴዎች ላይ እየሰሩ ለሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡

ዉጤታማ የሆነ የጥቆማና የቅሬታ ማስተናገጃ ዘዴዎችን ማዳበርና ጥቃት አድራሾችን መቅጣት ያስፈልጋል፡፡ ቅጣቶቹም ከማስጠንቀቂያዎችና ከገንዘብ ቅጣት ጀምሮ እስከ ህጋዊ እርምጃ ድረስ ያካተቱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የጥላቻ ንግግርና የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በቁጥር 1185/2012 የወጣዉ አዋጅ የጥላቻ ንግግርን አስከፊነት በመረዳት ለጥፋቱ እስር፣ የገንዘብ ቅጣትና ማህበራዊ አገልግሎትን የመሳሰሉ ቅጣቶች ደንግጓል፡፡ ግለሰቦች፣ ተቋማትና የህግ አካላት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ በቴክኖሎጂ ከታገዙ ጥቃቶች ጋር የተያያዙ ክሶችን በዚህ አዋጅ በመታገዝ ለተገቢዉ አካል እንዲያቀርቡ ሊደገፉ ይገባል፡፡

ከቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ጋር ትስስር በመፍጠር የጥቆማ ዘዴዎች ዉጤታማና የጥላቻ ንግግርና የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከወጣዉ አዋጅ ጋር አብረዉ የሚሄዱ መሆናቸዉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በአዋጁ መሰረት አንድ ማህበራዊ ሚዲያ መድረክ የጥላቻ ንግግርን ስርጭት የመቆጣጠርና የጥላቻ ይዘት ያላቸዉን ልጥፎች ሪፖርት በተደረጉ 24 ሰዓት ዉስጥ የማዉረድ ሃላፊነት አለበት (አንቀፅ 8.1፣8.2 እና 8.3)

### መተግበር

የ958/2016 ኮምፒዩተር ወንጀል አዋጅን መተግበር ያስፈልጋል፡፡ የዚህ አዋጅ አንቀፆች 12፣ 13፣ 14 እና 16 በቴክኖሎጂ ድጋፍ ከሚቃጡ ፆታን መሰረት ካደረጉ ጥቃቶች ጋር የሚገናኙ ድንጋጌዎችን የያዙና ግንዛቤን ለመፍጠርና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚጠቅሙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንቀፅ 12 ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆች ላይ ያነጣጠረ ማንኛዉም ወሲባዊ ባህሪያት (ይዘት ማዘጋጀት፣ ማሰራጨትና ምስሎች ማንሳት) እንደወንጀል ይደነግጋል፡፡ አንቀፅ 13 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ እንደፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች የሚታዩ ድርጊቶችን ይዟል፡፡ አንቀፅ 14 ደግሞ ከጥላቻ ንግግር ጋር የተያያዙ ጥፋቶችን ለመቆጣጠር ይጠቅማል፡፡ አንቀፅ 16 ደግሞ በአንቀፆች 14-15 የተደነገጉትን የሚጥሱ ይዘቶችን ያሰራጩ ወይም ለይዘቶቹ ምላሽ ያልሰጡ አገልግሎት ሰጪዎችን ተጠያቂ ያደርጋል፡፡ ይህም በቴክኖሎጂ በሚቃጡ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ተጠያቂነትን ለማስፈን መንገድ ይከፍታል፡፡

### ብቁ ማድረግ

በጥላቻ ንግግር፣ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች፣ በቴክኖሎጂና ፈጠራ ወይም በሴቶች መብት ዙሪያ የሚሰሩ ግለሰቦች (ዳኞች ፣ጠበቃዎች፣ፖሊሶች እና የመንግስት ሚንስትሮችን ጨምሮ) በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉጥቃቶችን ለመመርመር፣ ለመለየት፣ ለመጠቆምና ክስ ለመመስረት እዉቀት ማግኘትና ብቁ መሆን አለባቸዉ።



# ፫. ማህበረሰብ-መር ምላሾች

ሁሉም ጎጂ የሆኑ የኢንተርኔት ላይ ባህሪያትን በመጠቀምና የኢንተርኔት ላይ ጥቃት የደረሰባቸዉን ግለሰቦች በመደገፍ የኢንተርኔት መድረክ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ይችላል። ጥቃቶች ሲፈፀሙ ቆሞ ተመልካች ከመሆን ይልቅ በጉዳዩ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆን ያስፈልጋል።



## ማህበረሰብ መገንባት

በቁጥር ዉስጥ ሃይል አለ። ጥቃት አድራሾች ከቡድኖች ይልቅ ግለሰቦችን ኢላማ ያደርጋሉ። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች አላማ፣ የጥቃቱ ኢላማዎችን ዝም ማሰኘት፣ ከተለያዩ መድረኮች ላይ ገፍቶ ማስወጣት፣ የተወሰኑ የተሳሳቱ ወይም የተዛቡ አመለካከቶችንና እምነቶችን ማስቀጠልና ፍርሃትን መፍጠር ናቸዉ። በኢንተርኔት ላይ ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግር ይዘቶችን ሪፖርት ለማድረግ የሰዎች ቅንጅት መፍጠር ለጥቃቱ ሰለባዎች የአንድነት ስሜትን ለመፍጠርና የጥላቻ ንግግር ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ ያስችላል።

## ገንቢ ትርክቶችን መፍጠር

ለጥቃት አዘል ይዘቶች በሚከተለዉ መልኩ ምላሽ መስጠት

- በፆታዊ ሚና ዙሪያ ያሉ አፈታሪኮችን፣ የተሳሳቱና የተዛቡ አመለካከቶችን ማጋለጥ
- ማስረጃን መሰረት ያደረጉ መረጃዎችና አዉዶችን በማቅረብ ጎጂ የሆኑ ይዘቶችን መሞገትና የሚሰራጩ ሀሰተኛ መረጃዎችን ማረም
- አካባቢያዊ ምሳሌዎችን በመጠቀም ከጎጂ ትርክቶች ተቃራኒ የሆኑ ትርክቶችን መፍጠር (ለምሳሌ የሴቶች መብት ኢትዮጵያዊ እሴቶች እንደሆኑ የሚያሳዩ)
- በልጥፎቹ ላይ ገንቢና ጥሩ የሆኑ አስተያየቶችን በመስጠት የንግግሮቹን አቅጣጫ ማስቀየር
- ሃሽታጎችን ለጠቃሚ ጉዳይ እንዲዉሉ መቆጣጠር
- ጎጂ ይዘቶችን ተፅዕኗቸዉንና ጉዳታቸዉን በግልፅ በሚያሳይ መልኩ ማጋራት
- የኢትዮጵያ አዋጆችን የሚጥሱ ይዘቶች መለየት፡ የጥላቻ ንግግር ወይም 958/2016 ኮምፒዩተር ወንጀል አዋጅ

## መለየት

ኢንተርኔት ላይ ስለምናያቸዉ ይዘቶች አስተዋይ መሆንና

- የኢንተርኔት ላይ ይዘቶች ስድብ፣ ዛቻና ፆታን መሰረት ያደረጉ የተሳሳቱ መረጃዎችን ሲይዙ መለየት
- በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በፅሁፉም ሆነ በምስላዊ ዘዴዎች ሊደርሱ እንደሚችሉ መረዳት
- በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ታዋቂ ሴቶችን፣ የሴቶች መብት ተሟጋች አክቲቪስቶችንና የፆታ እኩልነትን የሚደግፉ ግለሰቦች ላይ ብቻ ሳይሆን ማንኛዉም ማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ ላይ እንደሚደርስ መረዳት
- ጥቃት አዘል ይዘቶችን እንደተለመደ አድርጎ ወይም ችላ ብሎ ማለፍ እንደማይገባ መገንዘብ

## መጠቀም

- ይዘቱን ለተገቢዉ ማህበራዊ ሚዲያ መድረክ መጠቆም
- ኢንተርኔት ላይ ያለዉን ጥቃት ለመከላከል ድጋፍ መስጠት ለሚችሉ ድርጅቶችና ማህበረሰቦች ጥቆማ መስጠት
- ይዘቱን ለመጠቆም እንዲቀል በምስል ወይም በሌላ መንገድ በመረጃነት መያዝ
- አንዳንድ ግዜ ጥቃት አድራሹን ብሎክ ማድረግ የተሻለ አማራጭ ነዉ

## ድጋፍ

- የኢንተርኔት ላይ ጥቃት የሚደርስባቸዉን ግለሰቦች መደገፍ
- ጎጂ የሆነዉን ይዘት ለመቅበር ተለዋጭ ጥሩ የሆኑ ትርክቶችን ማቅረብ
- በጎጂውን ይዘት ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ አፈታሪኮችን መሞገት
- ጥሩ በሆኑ መድረኮችና ታማኝ በሆኑ ድምፆች ዙሪያ ያለዉን ግንዛቤ ማጠናከር
- ኢንተርኔት ላይ ያሉ ጎጂ ባህሪዎችን መሞገት

## ትኩረት

EWiKA

ሴታሴት POWER

ኢ.ት.መ.ባ.ሴ.ን EMWA

ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ሴቶችን በማገልገል!

More than two decades in serving women!

# 4. ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ተጠያቂነት

የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች በቴክኖሎጂ ድጋፍ ለሚቃጡ ፆታን መሠረት ላደረጉ ጥቃቶች መስፋፋት ዋነኛ ሚና ይጫወታሉ። ስለሆነም እነዚህ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለማስቀረት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን የመደገፍና ተጠያቂነትን የማስፈን ሃላፊነት አለባቸው።

## የአጠቃቀም ደንቦች

የማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎች ጎጂ በሆኑ የኢንተርኔት ይዘቶች ዙሪያ ያሉ ፖሊሲዎቻቸውንና የአጠቃቀም ደንቦቻቸውን ማስከበር ሲሳናቸው ይታያል። ፌስቡክ፣ቴሌግራምና ኤክስ በመድረኮቻቸው ላይ ፆታዊ ጥቃትን የሚከላከሉ ህጎች አሏቸው። ይሁን እንጂ ሲ.አይ.አር በእነዚህ መድረኮች ላይ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ተመልክቷል።

የማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎች በሰብዓዊ መብት ላይ ላተኮሩ የተሻሉ አሰራሮች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። ይህም በመድረኮቻቸው ላይ ደህንነት እንዲኖርና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ያደርጋል።

## የመጠቆሚያ መንገዶች

የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች መጠቆሚያ መንገዶችን ግልፅና ተደራሽ ማድረግ ይገባቸዋል። የቅሬታ አቅራቢዎችን ሚስጥራዊነት መጠበቅና የግል መረጃዎቻቸው እንዳይጋሩ ማድረግም ያስፈልጋል።

## ምላሽና ግልፀኝነት

ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ላደረጉ ጥቃቶች ምላሽ ካለመስጠትም አልፎ ጎጂ የሆኑትን ይዘቶችን ከማስወገድና አጥፊዎቹን ተጠያቂ ከማድረግ ይልቅ የተጎጂዎችን አካውንት ሲያግዱ ይስተዋላል። ይህም አሳዛኝ የሆኑ ክስተቶች እንዲከሰቱ ምክንያት ሆኗል። ለምሳሌ ማንነታቸውን ኢላማ አድረገው ከተለጠፉ ጎጂ የፌስቡክ ልጥፎች በኋላ የተገደሉትን የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ማዕረግ አማረን ማንሳት ይቻላል።

የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ላደረጉ ጥቃቶች የሚሰጡትን ምላሽና ችግሮቹን ለማስቀረት እየወሰዱ ስላሉት እርምጃግልፅ ሊያደርጉ ይገባል።

## አልጎሪዝሞች (ALGORITHMS)

ፊደላትን በምልክቶች በመቀየርና ፅሁፎችን በምስል አድርጎ ጎጂ መረጃዎችን የማሰራጨት ድርጊቶች እየተበራከቱ ስለመጡ ማህበራዊ ሚዲያዎች ያለውን የማህበራዊ መድረክ አልጎሪዝም ማሻሻል ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም አልጎሪዝሞቹ አግላይ የሆኑ ይዘቶችን የማያጎሉና ፍትሃዊነትን የሚሹ ቡድኖችን የማያገሉ እንደሆኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።



## የይዘት ቁጥጥር

ብዙ ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ጥቃት አዛል ይዘቶች ለመለየትና ለማስወገድ የተለያየ ይዘት መቆጣጠሪያ መንገዶችን ቢከተሉም በቂ ግን አይደሉም። ተጠያቂነትን የማስፈን ሃላፊነት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች የደረሰባቸው ተጎጂዎችና ግለሰቦች ላይ የተጣለ ነው። የይዘት መቆጣጠሪያ ዘዴዎች በተለያዩ መድረኮች ላይ ወጥነት የሚጎላቸውና አካባቢያዊ አውዶችን ያካተቱ አይደሉም ።

አውድን መሠረት ያደረጉ የቃላት ስብስቦችን በማዘጋጀት፣ በማከማቸትና በመጠቀም ጠብ ቀስቃሽና ጎጂ የሆኑ ልጥፎችን መለየት ያስፈልጋል። በጥልቀት ባልተጠኑ ቋንቋዎች ዙሪያ ያለው የይዘት ቁጥጥር አናሳ ነው። የህብትና የመረጃ ውስንነት ቢኖርም በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን መለየት እንደሚቻል ይህ ጥናት አሳይቷል።

ማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎች፣ በሀገር በቀል ድርጅቶች የሚዘጋጁና በማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ያሉጥላቻ ንግግሮችን በመቆጣጣር ዙሪያ ያጠነጠኑ ውይይቶችን ማዘጋጀት ወይም መደገፍ ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ ፌስቡክ የቴክኖሎጂ፣ የሰብዓዊ መብት እና የፖሊሲ ባለሙያዎችን በማሰባሰብ የተወሳሰቡ የጥላቻ ንግግሮችን የሚመረምር ቦርድ አቋቁሟል። እንደዚህ አይነት ተነሳሽነቶች ቀጣይነት ሊኖራቸው ይገባል።

# 5. የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎች

የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎች በፆታ ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ አስተሳሳቦችንና ፆታን መሠረት ያደረጉ ማግለሎችን በመከላከል የሴቶችንና የልጃገረዶችን ተሳትፎ ያበረታታሉ። በሲ.አይ.አር ቃለመጠይቅ ተሳታፊዎች መሠረት የትኛውም ማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ለሴቶች ደህንነቱ የተጠበቀ አይደለም። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች በማህበራዊ ሚዲያ ቢሰራጩም መነሻቸው ግን ከአስተሳሰቦችና እምነቶች የመነጨ ነው። በዚህም ምክንያት ግለሰቦችን ለማስተማርና ለማብቃት የግንዛቤ ማስጨበጥ ዘመቻዎች አስፈላጊ ናቸው።

## ለጥቃቶቹ የመልስ ምት መስጠት

ሴቶችና ልጃገረዶች "#getbackinthekitchen" የመሳሰሉ ጎጂ ይዘትን ለሚያሰራጩ ሃሽታጎች ጥሩና አነቃቂ የሆኑ መልዕክቶችን በሚያስተላልፉ ሃሽታጎች የመልስ ምት መስጠት ይችላሉ። ይሄው ዘዴ በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶችን ሚና የሚያጎሉ የግንኙነት ዘመቻዎችን ለማጎልበትና ጠቃሚ የሆኑ የትምህርትና ስልጠና እድሎችን ለማመቻቸት ሊጠቅም ይችላል።

ሴታዊት፣ የስዉዲን ኤምባሲ እና የተባበሩት መንግስታት ሴቶች ድርጅት በመተባበር '#WhatSheWore' ወይም #ምንለብሳነበር በሚል ርዕስ ያዘገጀት አዉደ ርዕይ ላይ የአስገድዶ መድፈር የደረሰባቸው ሴቶች በድርጊቱ ወቅት የለበሱትን ልብስ ከታሪካቸዉ ጋር በማጣመር አሳይቷል።

## ዘመቻዎች

ትኩረታቸዉ ግልፅ የሆኑ ዘመቻዎችን ማካሄድ። ለምሳሌ "16 Days of Activism Against Gender-Based Violence" በሚል የተደረገዉ ዘመቻ በኢትዮጵያ ዉስጥ ስለ ሴቶች መብትና በቴክኖሎጂ ድጋፍ ስለሚቃጡ ፆታን መሰረት ስላደረጉ ጥቃቶች ግንዛቤ ለሚፈጥሩ ብዙ ዝግጅቶች መነሻ ሆኗል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በኢትዮጵያ ዉስጥ በዲጅታል ቴክኖሎጂዎች ላይ የሴቶችን እኩል ውክልናና ከኢንተርኔት ላይ ጥቃት የመጠበቅ መብቶችን ለማስተዋወቅ ባዘጋጀዉ ዘመቻ ላይ "መድረኬ፣ መብቴ፣ ድምፄ' የሚል መፈክር ተጠቅሞም ነበር።

## የተፅዕኖ ፈጣሪዎች ማህበረሰብ መገንባት

በይዘት ፈጠራና ስርጭት የሚያግዙ የተፅዕኖ ፈጣሪዎች ማህበረሰብን በመገንባት ያለዉን የተሳሳተ ትርክት መቀየር። የማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ፈጣሪዎችን ፣ታዋቂ ግለሰቦችን፣ አትሌቶችን፣ የፓድካስትአዘጋጆችንና እና ቲክቶከሮችን መደበኛና ኢመደበኛ ባልሆነ ሁኔታ በማቀናጀት ፆታን መሰረት ያደረጉ እንቅፋቶችን የሚቃወሙ ፀረ-ፆታዊ ጥቃት የሆኑ ይዘቶችን እንዲያሰራጩ ማድረግ።

## ወንዶች ከሴቶች ጎን እንዲቆሙ ማበረታታት

ለፆታ እኩልነት የሚደረገዉ ትግል በሴቶችና ልጃገረዶች ቢመራም ከወንዶች ተሳትፎና ድጋፍ ዉጪ ሊሳካ አይችልም። ወንዶች የዲጅታሉ አለም ደህንነቱን የጠበቀ እንዲሆንና ጎጂ የሆኑ ባህሪያቶችን በመሞገት ረገድ ያላቸዉ ሚና ከፍተኛ ነዉ። "እሱ ለሷ" በመሳሰሉ በፆታዊ አኩልነት ዙሪያ ግንዛቤ በሚፈጥሩ ዘመቻዎች ላይ መሳተፍ ይችላሉ።

ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል በተደረገው የ16 ቀን አክትቪዝም ወቅት የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ተማጋቾች ማዕከል 'ንግግሯ ተግባሯ' በሚል ርዕስ ባዘጋጀው ሁነት ላይ ሽመልስ ገበየሁን ጨምሮ ሌሎች ግለሰቦች የሴቶች መብት የወንዶችም ትግል እንደሆነ በአፅንኦት ተናግረዋል ።

## ትኩረት







HeForShe

#WhatSheWore or #ምንለብሳነበር

ሴተዊት Setaweet
ለፆታ እኩልነት



# 6. ሴቶችና ልጃገረዶችን መደገፍ

ለጥቃቱ ተጎጂዎች ድጋፍ ማድረግ ጥቃቱን ባይመልሰውም ለሴቶችና ልጃገረዶች ስነልቦናዊና ማህበራዊ ድጋፍ ማድረግና ኢንተርኔት ላይ ራሳቸውን ከጥቃት ስለመከላከል ማስተማር ጠቃሚ ነው። በተጨማሪም ድጋፍ ሰጪ ማህበራትን ማቋቋምና ደህንነቱ የተጠበቀ የመጠቆሚያ ዘዴ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል ወሳኞች ነው።

## ድጋፍ ሰጪ ማህበራት

በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች የደረሰባቸው ወይም ኢላማ ሊሆኑ የሚችሉ ግለሰቦች ሊወያዩ የሚችሉበትን መድረኮች መፍጠር። እነዚህን ማህበሮችን በመጠቀም ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንተርኔት መድረክን ለመፍጠርና አሁን ያለውን ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ለመቃወም መስራት ያስፈልጋል። ይህንንለማድረግ "Hollaback!'s HeartMob project" እና "TrollBusters" ከተባሉ ለተጠቃሚዎች የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ጥቆማ ምላሽና የመልስ ምት የሚሰጡ ባለሙያዎች ካሏቸው ፕሮጀክቶች ሃሳብ መውሰድ ይቻላል።

## ደህንነቱ የተጠበቀ ጥቆማ

ሴቶችና ልጃገረዶች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ የሚጠቁሙበት፣ የድጋፍ ጥያቄዎቻቸውን የሚያቀርቡበት እና ጥያቄያቸውን ከኢንተርኔት ማህበረሰቡ ጋር የሚያጋሩበት መንገድ ያስፈልጋል። የጥቃት ጥቆማ መስጫው መንገድ (ለምሳሌ በሴታዊት እንደተዘጋጀው አይነት የመረጃ ሰብሳቢ መጠይቅ) ጥቃቱ የት እንደተፈፀመ (የትኛው መድረክ)፣ ጥቃቱ ምን አይነት እንደነበር እና ምን አይነት ድጋፍ እንደሚያስፈልግ የሚመዘግብ መሆን አለበት።

## የስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ድጋፍ

በአዕምሮ ጤንነት ድጋፎች ዙሪያ ያለው አግላይ አስተሳሰብ ሊወገድ እና ከፆታ እንፃር ሊታይ ይገባል። ሴቶችና ልጃገረዶች ወደ ስራ ቦታ እንዲገቡ ለመርዳት የማማከር አገልግሎትና ትምህርታዊ ድጋፎች ሊተገበሩ ይችላሉ።

## የዲጂታል ደህንነት

ስለ ዲጂታል ደህንነት ስልጠና መስጠት ለችግሩ መፍትሄ ባይሆንም ሴቶችና ልጃገረዶች ኢንተርኔት በሚጠቀሙበት ወቅት ተጨማሪ ጥበቃ እንዲያገኙ ያግዛል። አሁን ላይ ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ያሉት የዲጂታል አለም የደህንነት ስጋቶች ከወንዶች ስለሚለዩ ሴቶችና ልጃገረዶች በተለይም ጋዜጠኞችና ሴት የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ከስልጠናዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ።

## አካላዊ ደህንነት

አንዳንድ ጊዜ የጥቃት ተጎጂዎች ግላዊ መረጃዎቻቸው በኢንተርኔት ላይ ያለፍቃዳቸው ከተለቀቁባቸው በኋላ በቤታቸው ውስጥ መቆየት አይችሉም። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ማዕከልን ጨምሮ ሌሎች ድርጅቶች ለተጎጂዎች ተለዋጭ የመኖሪያ ቦታ ማዘጋጀትን ጨምሮ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋሉ። እነዚህ አገልግሎቶች ድጋፍ ሊያገኙ ይገባል።

## ድጋፍ እየሰጡ ያሉ ድርጅቶችና መረጃዎቻቸው

### ነፃ የስልክ መስመሮች

**6388፡** ሴታዊት(አለኝታ)
**8044፡** ማሪ ስቶፕስ፣ አገልግሎቶቹ በአማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ሶማልኛና ትግርኛ ይገኛሉ
**7711፡** የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር፣ አገልግሎቶች በአማርኛ፣ አፋን ኦሮሞና ትግርኛ ይገኛሉ

AFRICAN WOMEN'S DEVELOPMENT FUND

SAFE SISTERS

HER Internet

EHRDC

Protection

EHRDC Provides Physical, mental and economical support for human rights defenders in all regions of Ethiopia

ETHIOPIAN WOMEN HUMAN RIGHTS DEFENDERS NETWORK — EWHRDN

መራሒት

END VIOLENCE AGAINST WOMEN NOW!" #Orangetheworld

ሴታዊት Setaweet

Womankind Worldwide

THE CYBERSMILE FOUNDATION

Association for Women's Sanctuary

SHE E-SECURES

NIQU ETHIOPIA

# 7. ቀጣይነት ያላቸው ጥናቶች

በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠርት ያደረጉ ጥቃቶች የደረሰባቸውን ተጎጂዎች ባነጋገርንበት ወቅት በጉዳዩ ላይ እርምጃ ለመውሰድና አክትቪዚምን ለማካሄድ ያለው የመረጃ እጥረት እንቅፋት እንደሆነ ገልፀዋል። ይህ ጥናት አነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት ታስቦ የተሰራ ቢሆንም ለሌሎች ጥናቶች መነሻ የሚሆኑ ሃሳቦችንም አካቷል። ሴቶችና ልጃገረዶች በጉዳዩ ላይ ያላቸው ተሚጋችነት በማስረጃ ላይ የተመሰረተ እነዲሆን ተጨማሪ ጥናቶችን መደገፍ ያስፈልጋል።

## የሲ.አይ.አርን ጥናት ወደሌሎች ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ማስፋፋት

የቃለመጠይቅ ተሳታፊዎች የትኛዉም ማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዳልሆነ ገልፀዋል። ቁጥራዊ ጥናቱ ፌስቡክ፣ቴሌግራምና ኤክስ ላይ ያተኮረ ነበር። ተጨማሪ ጥናቶች ዩቲዩብና ቲክቶክን ጨምሮ ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮችን ሊዳስሱ ይችላሉ።

## የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችን መገንባት

የሲ.አይ.አር ቡድን በቁጥራዊ ጥናቱ ወቅት 7000 የሚሆኑል ጥፎችን ተርጉሟል። በዚህ መረጃ ላይ በመመርኮዝ የጥላቻ ንግግርን ሊለዩ የሚችሉ ሞዴሎችን መፍጠር ይቻላል። እንደዚህ አይነት የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች ለጥቆማ መስጫ መንገዶችመጋቢ ይሆናሉ።

## በአንድ ሁነት ላይ ያተኮሩ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች

ሌሎች ጥናቶች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ምርጫ፣ የፖለቲካ ተቃውሞ፣ ሀይማኖታዊ ሁነቶች ወይም ግጭቶችን ጨምሮ በሌሎች ሁነቶች ወቅት ያላቸዉን ልዩነት ሊያጠኑ ይችላሉ።

## ተጨማሪ የጥቃት ሰለባዎችን ማጥናት

የሲ.አይ.አር አይነታዊ ጥናት ከጋዜጠኝነት ሙያ፣ ከሰብአዊ መብት፣ አክቲቪዚምና ከማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ፈጣሪነት የተወጣጡና በኢትዮጵያ ማህበረሰብ ዉስጥ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ 14 ሴቶችን ቃለመጠይቅ በማድረግ የተሰራ ነበር። ብዙሃኑን የሚያካትትና ለህዝቡ ይፋ ሊደረግ የሚችል የጥናት ዘዴ በመጠቀም የተለያዩ አይነት ልምዶችን ማካተት ይቻላል።

## ያሉትን ህጎችና ፖሊሲዎችን መገምገም

በስራ ላይ ያሉ ህጎችን፣ ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን ዉጤታማነት መገምገም አስፈላጊ ነዉ። ተጨማሪ ጥናቶች ያሉትን ድክመቶች በመለየት ለሴቶችና ልጃገረዶች የሚሰጠውን ከለላ ሊያጠናክሩ ይችላሉ።

## የዲያስፖራዉ ሚና

በተደረጉት ዉይይቶችና አዉደ ጥናቶች ወቅት ዲያስፖራዉ ትርክቶችን በማስቀጠልና ኢንተርኔት ላይ ያሉ ይዘቶችን በማጉላት ዘንድ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት በሁሉም ዘንድ የተነሳ ሃሳብ ነዉ። እንደ ሃሳብ ሰጪዎቹ ይህ ሴቶችና ልጃገረዶችን ጨምሮ በሌሎች ማንነት ቡድኖች ላይ ጉዳት ያስከትላል። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን በመፈፀም ረገድ ኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉ ተጠቃሚዎችንና ዲያስፖራዎችን የሚያነፃፅሩ ተጨማሪ ጥናቶች ሊሰሩ ይችላሉ።

## አሁን ያሉ ፕሮጀክቶችን መገምገምና ጥምረት መፍጠር

ከተለያዩ የሲቪል ማህበረሰቦች ጋር በተደረገዉ ዉይይት ወቅት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል ያለሙ ፕሮጀክቶች እንዳሉ ግልፅ ነበር። እነዚህን ፕሮጀክቶች በመገምገም፣ የጋራ ነጥቦችን በመመርመር፣ መረጃ ልዉዉጥና ተፅዕኖዎችን ለማጠናከር በድርጅቶች መሃከል ጥምረት መፍጠር ይቻላል።

